# መልዕክት ለአባቶች/እናቶች በያላችሁበት

ከሰላማዊት አሰፋ

*«ማጠቃለያ «እናቴ» የምንላት ሀገራችን በወጓና በባህሏ ችግሮቿን የሚፈታ አስታራቂ ካጣች የአባቶች/እናቶች ሽበት ይነቀልና ሁላችንም ልጅ እንሁን። በልጅ ሆድ አስታራቂ የሚሻ ክፉ ነገር አያድርምና።»*

## ምነው አስታራቂ አጣን?

መቼም ይህንን ጥያቄ ያነሳሁት ያለ አንድ ምክንያት አይደለም። እንደ አንድ ኢትዮጵየዊ ወጣት ወይም ኢትዮጵያዊ ተወላጅና ቀጣይ የዛች ሀገር ተረካቢ ትውልድ በውጭ ያለው ወቅቱ ሁኔታ በተለይም በወቅቱ ፖለቲካና ፖለቲከኞች ምክንያት በሕብረተሰባችን ዙሪያ አልፎ አልፎ የሚንፀባረቀውን «የእሱ» «የእኔ» ወይም «የእኔ ብቻ» ባይነትን መንፈስ ስመለከት ስለሚያሳስበኝ ነው- አባቶች/እናቶች ተጠየቁ ማለቴ። በነገራችን ላይ ዋናው ትኩረቴ በውጭ ሀገር ይስተዋልኩት ነውና «የዛች ሀገር» ማለቴም ከዚሁ በመነሳት ነው።

ጽሑፌ አጭር በመሆኑ ሳልንደረደር ዘው ብዬ ወደ ጭብጤ ልግባ። አሁን አሁን የነገሮቻችን ማጠንጠኛ ሁሉ ጥላቻ እየሆነ ነው። ፖለቲካችው የጥላቻ፣ ስፖርታችን የጥላቻ፣ ሙዚቃችን የጥላቻ ... ባህላችንም ያው እየሆነ ይመስለኛል። ለሁሉም ነገራችን ቦታ የሌለን ወይም የማንመርጥ እየሆን ነው። በተለይ ግን ፖለቲካችን መላቅጡን አጥቶ ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ እየገባ አላላውስ ብሎናል። ማህበራዊ ግንኙነቶቻችንን ሳይቀር በጥላቻ እየነቀዘ ነው።

ሚዲያው (በተለይም ኤሌክትሮኒክሱ) በሊበራሊዝም የማህበራዊ አስተሳሰብ ውስጥ እውቀቱ ባለው ባለሙያ ስር ሳይሆን ባገኘበት በጥላቻ የባርነት ቀንበር ስር ወድቋል። ሙያዊ ስነምግባሩ (Professional Ethics) በዞርንበት ባይደርስ እንኳ የየሚዲያው ጋዜጠኛ አንዱ ሌላውን «የሀገር ልጅ የማር እጅ» የሚለው ብሂል ረስቶ፤ እህት ወንድሙ መሆኑን ዘናግቶ በሌላው ላይ ያለው፣ ያሰበውን፣ የሰማውን አንዳንዴም የሌላውን ሁሉ ፈጥሮ በመሰለው መንገድ ያወርደዋል። አገር ውስጥ አንድ ኢትዮጵያ በውጭ ሀገር ደግሞ ሌላ የማናውቃት አንድ ኢትዮጵያ በሚዲያው ተፈጥራለች። ፖለቲካችን ከአገርና ከክልል አልፎ ዛሬ በእያንዳንዳችን የግል ቤት ውስጥ ገብቷል። ባል-ሚስት፤ ልጅ-አዋቂ ሳይል ... ሁሉም ፖለቲከኛ ብቻ ሳይሆን እራሱ ፖለቲካ ሆነናል። ከዚህም አልፎ ባፍ ባፍንጫችን ገብቶ አንጀታችን ውስጥ ከፍ ሲልም ሕሌናችን ውስጥ አካል ሰርቶ «እቱ ገሜ» ይጫወት ጀምሯል።

«ምሑሩ» ሳይቀር የራሱን ባላንጣ እየፈጠረ ጠብ ያለሽ በዳቦ በቃላት የእንካ ሰላምቲያ.. በምንቲያ ትግትግ እያካሄደ ነው። አንዳንዴም ከምሑራዊ አንደበት በግድ ዘለው ወይም

አምልጠው ወይም ተመንጥቀው ሊወጡ የማይችሉ ቃላቶች ብቻ ሳይሆን ሃሳቦችና አስተሳሰቦች እየወጠ ነው:: ሙት መቀስቀስ አይሁንብኝ እንጂ አበው በክብር ለዘመናት ካረፉበት መሬት ፈንቅለው ቢነሱና በመለከቱን «ትምህርት ለምኔ» እንደሚሉ እርግጠኛ በሆን ነበር:: ስሜታዊነት ገኖ አስተዋይነት ገልዋል:: በዚህም ምሁሩን ከሌላው የሕብረተሰብ ክፍሉ የሚለዩት ምሑራዊ ባህሪያ ሁሉ እየጠፉ ነው:: አስተዋይነት፣ አመዛዛኝነት፣ ታጋሽነት፣ ለዘብተኝነት፣ ይቅር ባይነት፣ ... ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ እየራቁን ነው:: የመደብ ትግሉንም በቃላት ጦርነት የለኮሱም ማርክሲስቶች አሉ::

በሀገር ቤትም (ከምንሰማው) ሆነ በውጭ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉም ለአንድ አገርና በአንድ አገር አገራዊ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ መሆናቸውን መገመት እስከሚቸግር ድረስ ከመወያየት ይልቅ ንትርክን፣ ከመስማማት ይልቅ ጭቅጭቅን፣ ከመነጋገር ይልቅ ኩርፊያን በሰፊው የተያያዙበትን ትዕይንት እያስተዋልን ነው:: በሀገር ውስጥ በተለይ በውጭ በአካላዊ መቀመጫችን ሳይሆን በልባችን ቁጭ ብልን መነጋገር መደማመጥ ተስኖን በኩርፊያ ጠላቶቻችን ጉያ ስር ወጥተን እንሸጎጣለን:: ቆም ብለን ማሰብ እያቃተን ነው:: ጊዜ ሰጥተን ሌላውን ወገን መስማት እየተሳነን ነው:: መወነጃጀል፤ መዘላለፍና ስድብ ልማዳችን ባህላችንም እየመሰለ ነው:: ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ ተመልካች እንጂ ከልካይ፤ አስታራቂ አልታየም::

ወደሀገር ውስጥ ብንመለከት የሀገሪቱ የሥልጣን ቁንጮ በሆነው በአንድ ምክር ቤት ውስጥ የተሰየሙት እንኳ ትልቁ የመንግስት ስልጣን እነሱው መሆናቸውን ዘንግተውት እንደ አንድ ግኡዝ አካል «መንግስት!» በሚል ፈሊጥ ለችግሮች ሁሉ መንግስትን ተጠያቂ ያደርጋሉ:: በዚህ እሳቤም በአንድ አገራዊ ጉዳይ ላይ ሙሉ በሙሉ የተስማሙበትን ጊዜ እስካሁን እንደናፈቅን ነው:: የፖለቲካ መሪዎች ከወከሉት ሕዝብ ፍላጉት ይልቅ «የኔ» «ያንተ» በሚል መንፈስ የራሳቸውን የግል ፍላጐት ብቻ በሰፊው ሲያራምዱ ይታያል:: «ጥላቻ» የሚሉት የፖለቲካ ካንሰር እጅና እግራችንን ጠፍሮ ይዞ አላላውስ ብሎናል:: ሁሉም ከራሱ መጠናከር ይልቅ የሌላውን ወድቆ ማየት ይናፍቃል:: ያሻው፤ ያሰበውን ሁሉ ያለማንም «ተው ባዬ» ያደርጋል::

በውጭ ያለው ዜጋና ተወላጅም የስደት ሕይወት በእራሷ ቁልቁል የምትኮረኩመው አንሶት እርስ በእርሱ ውስጥ ውስጡን ይኮራኮማል፣ ይጉሻሸማል:: ፖለቲካችን እንደጨው የማይገባበት የለም:: ማህበረሰቡ በጋራ ጉዳይ ይቅርና በአገር ጉዳይ ላይ ሊተባበር እንዳይችል እያደረገ ነው:: በራሱ የጋራ ጉዳይ ላይ በ«የኔ»«ያንተ» ፈሊጥ የጐሪጥ ይተያያል:: በውጭ ያለው ተገናኝቶ አለመተማመን፣ በችግር አለመረዳዳት፣ በጋራ ጉዳዮች አለመተባበር ዛሬ እንደ ሀገር ቤቱ የሚያሳፍሩ አይደሉም ብቻ ሳይሆን እነዚህ ድንቅ ባህሎቻችን ወደ ነበሩ እየተቀየሩ ነው ማለት ይቻላል:: ይህ ሁሉ እየሆነ ደግሞ አሁንም «ተው ባይ» ከልካይና አስታራቂ ሳይሆን ግፋ ባይ እየበዛ ነው::

ከ97 ምርጫ ዋዜማ በፊት የተሰባሰቡ «ዲሞክራት» ሁላ ልዩነቶቻችንን አቻችለን በአክሲዮን እንታገል ብለው የመሠረቱት ፓርቲ በምርጫ ማግስት በፖለቲከኞች አለመቻቻል እንደዶሮ ብልት ሲገነጣጠልም ተው ባይ-አስታራቂ አልነበረም:: ይባስ ብሎም «ዲሙን በዲሞትፈር» የሚለውን መፈክር አንስተን አንድ ትውልድ እንዳልሰዋን ዛሬም «ፋኖ ተሰማራ» የሚልም ብቅ እያለ ባለበት ወቅት አሁንም ተው ባይ የለም::

በሀገር ውስጥ ያሉና በጋራ ተባብረን በራሳችን መፍታት የምንችላቸውን ችግሮች ወደ ውጭ አምጥተን እያወሳሰብንና መጪው ትውልድ እንኳ እንዳይፈታቸው ውሉን እያጠፋን ነው:: ቅንጅትንም ወደውጭ አምጥተን «የእኔ» «የእሱ» ብለን በታተነው ወይም ሲበተን ተው የሚል አባት/እናት እስካሁንም አላየንም:: «የእኔ» «የእሱ» በሚል ፈሊጣችን እጥረቶቻችን ለመሸፈን፣ ክፍተቶቻችን ለመሙላት ሌላው ቀርቶ እርዳታ በሚሹ ማህበረሰባችን ወገኖቻችን መሆናቸውን ዘንግተነው «የእኔ» «የአንተ» በሚል ፈሊጣችን ተጠምደን እንዳይረዱ ለማድረግ ስንጠላለፍ አይተናል:: የእኛው የወገን ድጋፍና እርዳታ ቀርቶ የሌሎች እንዲደርሳቸው እንኳን ከመርዳት ይልቅ የምናደናቅፍበትን ሁኔታ በግልፅ ታዝበን አልፈናል:: እንዳይረዱም አድርገናል:: አሁንም ያው ነው:: ነገር ግን አሁንም ተው ባይ የለም::

«ስም ይወጣል ከቤት ይተላለፋል ወደ ጐረቤት» እንዲሉ ሆኖ የእኛው አንሶ ደግሞ «ወዳጆቻችን» -(-ጠላቶቻችን ላለማለት ነው-) «ውሻ በቀደደው ጅብ ... » እንዲሉ እኛው የፈጠርናቸውን ቀዳዳ እየተጠቀሙ የጥፋት መረባቸውን ጥለው፣ ኢላማቸውን አነጣጥረው እኛኑ በእኛው ላይ በመተኮስ የበለጠ እያራራቁን፣ እያለያዩን ነው:: ባይሳካ እንኳን አሁንም እየሞከሩ ነው:: ለዚህ ደግሞ ታላላቆቹ ቢቀሩ እንኳን ትላንት የተወለደችው ትንሿ «ወዳጃችን» እንኳን ቆማ መራመድ ሳትችል በዳዴ እየሄደች ከሌሎች ተሻርካ እየፈፀመችብን ያለውን ተግባር አይናችንን ለአንድ አፍታ ጨፍነን በሕሊናችን ብንመለከተው ሊያሳስበን የሚገባ ተግባር በነበረ ነበር:: ይህ ሁሉ እየሆነ ደግሞ አሁን ተው ባይ የለም:: ይልቁንም «በኢትዮጵያ ትቅደም» መነጽር በአንድ አይናችን ብቻ ወደፊት እያየን፤ «አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት»ን እየዘመርን አንድ ዘመንና አንድ ትውልድ እንዳላሰለፍን ዛሬም «በዲሞክራሲ» ስም ወደመጣንበት ጐዳና ስንመለስም ተው ባይ አባት-እናት የለም::

ሌላው ቀርቶ የአንድነታችን፣ የመቻቻል ባህላችን፣ የመተባበርና የመተጋገዝ ልምዳችንና የሀገር ፍቅራችን መግለጫ የሆነው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችንን በሚመለከት እንኳ «የእሱ» «የእኔ» እየተባባለ ነው:: የአገራችን ጠላቶች ብሔራዊ አንድነታችንና ጥቅማችን ላይ ጥቃት ሲቃጡ አንድ «የእኔ» «ያንተ» በሚል መንፈስ አንድ ያልሆንበት ጊዜ ተስተውሎም ነበር:: ይህ ሁሉ ሲሆንም ተው ባይ የለም:: ከተመልካች በቀር ከልካይ፣ አስታራቂ ወይም መካሪ የለም:: አሁንም ሁሉም ድራማውን በሚመስለው መልኩ እየተጫወተ እራሱ በሚመስለው መልኩ እየተመለከተው ነው:: እንግዲህ እነዚህና ሌሎችም ናቸው ምነው አስታራቂ ሽማግሌ አጣን? የሚለውን ለመጠየቅ ያስገደደኝ::

አባቶቻችንና ወላጆቻችን በነበራቸው አቅም የተጣላን አስታርቀው፣ አፈንጋጭን መክረውና ገስፀው፣ በሕይወት የሚከፈለውን ሁሉ ከፍለው ፍቅርን፣ ክብርን፣ አንድነትን አስረክበውን አልፈዋል። ነገር ግን የታሪክ ቅብብሎሹ አላበቃም። ረጅምና ወጣ ገባ መንገድ ከፊታችን ተደቅኖ ይጠብቀናል። ለዚህ ጉዞ መተባበር፣ መተጋገዝ፣ ልብ ለልብ መገናኘት ይኖርብን ነበር። በሀገራችን ሁላችንም ያገባናል ብለን መግባትና መግባባት፣ ከመራራቅ ይልቅ መቀራረብ፣ ከመጣላት ይልቅ መፋቀር፣ ከመኳረፍ ይልቅ መስማማትና መተላለፍ ይገባን ነበር። ለዚህ ደግሞ በየምንኖርበት ሀገራት ሁሉ ከሚያስታርቅ ሽማግሌ የሚያስታርቀን ሃሳብ ፤ ልዩነቶች ወደ አለመግባባት በሚሄዱበት ቦታ ሁሉ ያስፈልገን ነበር። ነገር ግን ልዩነቶች ተፈጥረው አለመቻቻል ሲያስከትሉ ተው ባይ አስታራቂ እስካሁን የለም። ለመጪው ትውልድ የተሻለ ሀገር፣ የተሻለ የመቻቻልና የመከባበር ቀና መንፈስ ለማስረከብ የሚያስብ ወይም የሚሞክር አባትና እናት አስታራቂዎች ጭራሽ የሌለንና ያልተፈጠሩ ያህል እየተሰማን ነው። ያሁኑ ትውልድ ከአባቶች ምን ይረከብ? የሚለው ግራ ገብቶናል። ምነው አስታራቂ ታጣ? የብዙ ዘመናት ታሪኳና ባህሏ ሁሉ አልፎ አሁን ሀገራችን አስታራቂ ያጣችበት ዘመን መጣ ይሆን? መልሱን ከአባቶች/ከእናቶች እንጠብቃለን። በእኔ በኩል ግን «እናቴ» የምንላት ሀገራችን በወጓና በባህሏ ችግሮቿን የሚፈታ አስታራቂ ካጣች የአባቶች ሽበት ይነቀልና ሁላችንም ልጅ እንሁን። በልጅ ሆድ አስታራቂ የሚሻ ቂም አያድርምና።

Selamawit Asefa (selam23as@yahoo.com)
Department of Political Science, University of Delaware